

**ஐ42-1ஜ**

# በሰጠን አዕምሮ እንጠቀም

## አዕምሮአችንን እንቅረጽ

የእግዚአብሔርን ሥራ በተቀላጠፈና በአማረ መልክ ለመሥራት ጥበብና ዕውቀት ያስፈልገናል። ያለጥበብ ለመ ሥራት መሞከር በደነዘ መጥረቢያ እንጨትን ለመቁረጥ እንደ መሞከር ይሆናል። “የደነዘዘ መጥረቢያውን የማይስል ሰው ኃይሉን በከንቱ ይጨርሳል፤ ስለዚህ ጥሩ ውጤት ለማግኘት በጥበብ መሥራት ያስፈልጋል” ይላል መክብብ 10፥10።

## ሰባኪ አሰባበኩን ያሻሽል

ሰባኪ ቃሉን የመስበክ ኃላፊነት አለበት (2 ጢሞ. 4፥2)። መስበክ ደስ የሚለው ብቻ ብድግ ብሎ የሚያደርገው ነገር አይደለም። በጥበብና በዕውቀት ራሱን ለማሳደግ ጥረት ሳያደርግ የሰለቸ፣ የተለመደ፣ የማይጣፍጥ፣ እንቅልፍ የሚያስመጣ ስብከት የሚሰብክ ከሆነ ፍሬ የለውም። “እኔ ባዶ ሸምበቆ ነኝ፤ እኔ ምንም የለኝም፤ ጌታ ብቻ በውስጤ ይናገር” ብሎ ያለዝግጅት ለመስበክ የሚቀርብ ሰባኪ፥ ኃላፊነቱን የረሳ አገልጋይ ነው። በየቦታው የምንሰማቸው አንዳንድ ስብከቶች ጥልቀት የጎደላቸው፣ ምንም ትምህርት የሌላቸው ዝግጅት የጎደላቸው ናቸው። እኛ ሰባኪዎች መስበካችንን ነው እንጂ ስብከታችን ምን ያህል እንደሚጥመው ወይንም ተደጋጋሚ በመሆኑ እንደሚሰለች የምናውቅበት መንገድ የለንም። ብዙ ጊዜ የምንሰማው አስተያየት፥ በአካባቢያችን ሆነው “የሚያጨበጭቡልንን” ሰዎች ብቻ ነው። በተለይ ኢትዮጵያውያን በተፈጥሮአችን የሚሰማንን ለመናገር ድፍረት ስለሌለን “በስብከትህ ምንም ዓይነት ፍሬ ነገር አላገኘሁበትም” ብሎ በድፍረት የሚነግረን የለንም። ድፍረት ኖሮአቸው ቢነግሩንም እንኳን አስታያየታቸውን መቀበላችንን እጠራጠራለሁ።

አንዳንድ ሰባኪዎች ራሳቸውን በማሻሻል ፈንታ የሕዝቡን ስሜት ለመሳብ አቋራጭ መንገድ ይጠቀማሉ። እርግጥ ነው በእምነታቸውና በአስተሳሰባቸው ያልበሰሉ አንዳንድ አማኞች ነገሩ ሳይገባቸው ሊያጨበጭቡላቸው ይችላሉ፤ የበሰሉትና በክርስትና ሕይወት ውስጥ የቆዩት ግን፥ ሰባኪው በቂ ዝግጅት እንደሌለውና ሃሳቡን ዝም ብሎ እንደሚደጋግም በቀላሉ ማየት ይችላሉ። አሰባበኩን በማሻሻል ፈንታ ተቀባይነት ያሰጡኛል ብሎ የሚገምታቸውን አንዳንድ ዘዴዎችን ሲጠቀም ይታያል።

ሀ) በመጮሁ ስብከቱ ኃይል የሚያገኝ ስለሚመስለው ያለአግባብ ያለቦታው ያለቅጥ ይጮሃል። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ድምጹ አንድ ዓይነት ስለሆነ ለሚሰማው እጅግ ይሰለቻል። አሜሪካ ውስጥ ያሉ አንዳንድ የጥቁሮች ቤተ ክርስትያናት የሰባኪያቸውና ችሎታና አሰባበክ የሚለኩት ሰባኪው በሚይሰማው ጩኸት እንደሆነ ቀረብ ብለን ያወቅናቸው ጥሩ አሜሪካውያን ሰባኪዎች አጫውተውናል። እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ጥሩ ስብከት መሆኑ የምንመዝነው ሰባኪው በሚያሰማው ጩኸት እንዳልሆነ እርግጠኞች ነው።

ለ) በቂ ዝግጅትና ጥናት የሌለው ሰባኪ ለሕዝቡ የሚሰጠው አዲስ ነገር ስለማይኖረው “እኔ አልናገርም፤ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ይናገራል” በማለት በሕዝብ ፊት ባዶውን ይቀርባል። የሚያሳዝነው መንፈስ ቅዱስ እየሠራ መሆኑን ለማሳየት አዲስ ሰዎችን የሚያስደነግጥ የቆዩትን ደግሞ የሚያስገርም መድረኩ ላይ ጭፈራ ማሳየት ይጀምራል። አዲስ አማኞች ወይንም በእምነታቸው ያላደጉ ምኑንም የማያውቁ “አቤት ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን ተንቀሳቀሰ” ይሉ ይሆናል። የቆዩ አማኞች ግን ከጩኸትና ከጭፈራ በስተቀር ፍሬ ነገር አያገኙበትም። እነርሱም ቅሬታቸውን ቢያሰሙ “መንፈስ ቅዱስን ይቃወማል እባላለሁ” ብለው ስለሚፈሩ አፋቸውን ዘግተው በቅሬታ ይቀመጣሉ።

ሐ) ሰባኪው ድክመቱንና ስንፍናውን የሚያሸንፍበት የራሱ ሌላ ዘዴ አለው። “በሰው ዕውቀትና ጥበብ ወንጌልን አልሰብክም፤ መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝን ብቻ ነው” በማለት ዕውቀትንና ጥበብን እያጥላላ መናገር ይጀምራል።

## አገልግሎታችንን ለማሳደግ የምንወስደው እርምጃ

ሀ) የሰባኪያንን ችሎታ ለማሳደግ፥ ስብከታችንን የበለጠ ለማሻሻል አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልገናል፥

1. ሰባኪዎች እየተገናኙ እርስ በርሳቸው ገንቢ ሂስ ወይንም አስተያየት የሚለዋወጡበት ስብሰባዎችና ፕሮግራሞች ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ስብሰባው እርስ በርስ ለመሞጋገስ ሳይሆን፥ እርማት የሚያስፈልገውን ለማረምና ለማስተካከል መሆን አለበት።

2. አብዛኛዎቻችን እርግጥ ሰባኪዎቻችን የሆንነው ትምህርት ቤት ገብተን ሳይሆን በግል ልምምድ ብቻ ነው። በወቅቱ እራሳችንን ለማስተማር ዕድልም ሆነ ጊዜ አልነበረንም። ባለን ተጠቅመን፣ ጌታም ልባችንን አይቶ ፍሬ እንድናፈራ አደረገን። ይሁን እንጂ ትምህርት አያስፈልገንም፣ እራሳችንን ማሻሻል የለብንም ማለት አይደለም። አሁን ዕድሉና ጊዜው ስላለን እራሳችንን ማሻሻል የግድ ያስፍፈልገናል። "እኔ ብዙ ጊዜ ሰብኬአለሁ ማንም እኔን ስለ አሰባበክ ሊያስተምረኝ የሚችል ሰው የለም" ማለት ደካማነት ነው። ማናችንም አድገን የበቃን የለንም፤ ገና ብዙ ይቀረናል።

3. በክርስትና ሕይወታቸው ያደጉ ምዕመናን አሰባበካችንን እንደገመግሙና አስተየየት እንዲሰጡ ፎርም አዘጋጅተን እንስጣቸው። የዚህም ዓላማ ጥሩ ሰባኪነታችንን እንዲያረጋግጡልን ሳይሆን፥ ማስተካከል ያለብንን ማስተካከል እንድንችል ድካማችንን እንዲጠቁሙን ነው።

4. ብዙ ጊዜ ሰባኪዎች ከራሳችን በስተቀር ሌሎች ሰባኪዎችን መስማት አንፈልግም። ብንሰማም በማድነቅ ሳይሆን በማጥላላት ነው። ይሄም አለመብሰላችንን ያሳያል። ስብከታችንን ለማሻሻል ከፈለግን፥ ሌሎች ሰባኪዎች ሲሰብኩ በአካል ተገኝተን ማዳመጥ፣ ካልቻልን ደግሞ በካሴት፣ በቪዲዮ የተቀረጹትን የተለያዩ ሰባኪዎችን ስብከት መስማት ይጠቅመናል። ዓላማው እነርሱን ኮርጀን እንደ እነርሱ ለመስበክ ሳይሆን፥ ከያንዳንዳቸው የተለያየ ጥሩ ትምህርት ለማግኘት እንድንችል ነው። አንዳንዶቻችን "እኔ ከማንም መማር አልፈልግም፤ የእኔ አስተማሪዬ መንፈስ ቅዱስ ነው" እንል ይሆናል። ይሄ አባባል መነፍሳዊነት ሳይሆን ከሌላው ለመማር ያለመፈለጋችንን የሚያሳይ የትዕቢት መንፈስ ነው።

ለ) መዝሙሮቻችንን ለማሻሻል

በኢትዮጵያውያን በየጊዜው ስለሚወጡት ጥሩ ጥሩ መዝሙሮች ደስ ይለናል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ድክመት ይታይባቸዋል። አንዳንዶቹ ዜማቸው ከግጥሙ ጋር አይሄዱም። አንዳንዱ ደግሞ ቋንቋው ትክክለኛ የሥነ መለኮት ሀሳብ የያዘ አይደለም። አንዳንዱ ደግሞ ዘፈን ይመስላል የሚል አስተያየት አለ። እነዚህ ያሉንን ጥሩ ጥሩ መንፈሳዊ መዝሙሮች የበለጠ ጥራት ለመስጠት አንዳንድ መደረግ ያለባቸውን ሃሳቦች ለመሰንዘር እንሞክራለን።

1) የመዝሙር አገልግሎት ያላቸው ወገኖቻችን፥ በመንፈሳዊ የሙዚቃ ትምህርት፣ በዩንቨርሲቲ ደረጃ ከተማሩ ወገኖቻችን ጋር እየተገናኙ ቢወያዩ፣ አንዱ ከሌላው ዕውቀትና ልምምድ ለመማር ቢችል የመንፈሳዊ ሙዚቃ ደረጃችን ምን ያህል ከፍ ባለ ነበር። "በሙዚቃ ትምህርት ዲግሪ ባይኖረኝም ምንም የጎደለኝ ነገር የለም" በማለት እራስን ለማሻሻል አለመሞከር ደካማነት ነው።

2) በተለይ የሙዚቃ ተሰጦ ያላቸውን ወገኖቻችን ውጪ አገር ሄደው የሙዚቃ ትምህርት መማር የሚችሉበትን መንገድ ቤተ ክርስትያን ማመቻቸት አለባት። ነገሩ ከባድ ይምሰል እንጂ በአገር ደርጃ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፥ ከታሰበበት መንገድ አይጠፋም። ለመሆኑ በመንፈሳዊ የሙዚቃ ትምህርት የተማሩ መዝሙሮቻችንን የሙዚቃ ኖት እንዲኖራቸው ሊያደርጉ የሚችሉ ምን ያህል ሰዎች አሉን? መልሱ ስውር አይደለም።

3) አንዳንድ መዝሙሮች ዜማቸው ጥሩ ይሆንና መልዕክቱ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አይደለም። የመልዕክቱ መለኮታዊ ሃሳብ (theology) ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በሙያው ትምህርት ያላቸው ወገኖቻችን እንዲያዩት ማድረግ ይረዳል።

4) በልዩ ልዩ አብያተ ክርስትያናት በመዝሙር አገልግሎት የሚያገለግሉ ወገኖች ተገኝተው የሚማሩበት ሃሳብ ለሃሳብ የሚለዋወጡበት ሴሚናር ወይንም የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት።

ሐ) የቪዲዮና የካሴት መልዕክታችንን ለማሻሻል

መልዕክቶችን በቪዲዮና በካሴት መቅረጽ አገልግሎታቸው ያደረጉትን ወገኖቻችንን ስናይ ደስ ይለናል። ጥረታቸውን ስናይ ደስ ይለናል። ይሁን እንጂ የሥራቸው ጥራት ብዙ ይቀረዋል። በቁጥር ብዙ አይሁን እንጂ አንዳንድ ወንድሞች በቪዲዮና በፊልም አነሳስ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተምረው በዲግሪ የተመረቁ በመካከላችን ብቅ እያሉ ነው። የጌታን ወንጌል ለማሰራጨት የቪዲዮ ኃይል ያለውን አቅም እያወቅን፥ ረጅም ዘመን በሙያው የሰለጠኑትን ወገኖቻችንን የአገልግሎት ዕድል አለመስጠት፣ አለማበረታታት ትልቅ የሰው ኃይል ማበላሸት ይሆናል። በግል ልምምድ ብቻ በዚህ አገልግሎት የተሰማሩ ወገኖች ከነዚህ ከፍተኛ ትምህርት ከቀሰሙ ሰዎች ጋር ተገናኝተው ቢወያዩ፣ ቢማሩ አገልግሎታቸው የበለጠ ጥራትና ኃይል ይኖረው ነበር።

## ሰፊ ልምምድ ባላቸው ሰዎች ለምን አንጠቀምም?

በየጊዜው ሰፊ የሆነ የሕይወት፣ የሥራ ልምምድና ሰፊ ትምህርት ያላቸው አዳዲስ ነፍሳት እየተጨርሙ ናቸው። ቤተ ክርስትያን ለእነዚህ ወገኖች የአገልግሎት ዕድል በመስጠት ፋንታ፥ የእግዚአብሔር ሥራ “በጥበብና በዕውቀት” አይሠራም በማለት የአገልግሎት ዕድል መከልከሉ ደካማነት ነው። ቤተ ክርስትያን ውስጥ በዕድሜ፣ በደረጃ፣ በትምህርት፣ በአስተሳሰብ የተለየዩ ሰዎች ይኖራሉ። እርግጥ ነው በጌታ ፊት ሁሉም እኩል ናቸው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ምርጫ፣ አቋምና የሕይወት ፍልስፍና አለው። ስለሆነም በሀሳብ፣ በፍልስፍና የሚቀራረቡ ሰዎች ተገናኝተው የእግዚአ ብሔርን መግሥት ለማስፋፋት ምን ዓይነት ድርሻ እንደሚኖራቸው እንዲወያዩ ማድረግ ትልቅ ጥበብ ነው። የቤተ ክርስትያን መሪዎች ለብቻቸው ከሚታገሉና ከሚደክሙ፣ ሌሎችን በአገልግሎት እንዲሰለፉ ቢያደርጉ ሥራቸው ይበልጥ ፍሬያማ ይሆናል። “ዕውቀት ያልተጨመረበት ትጋት ጠቃሚ አይደለም” (ምሳሌ 19፥2)።

## ለምን ባለ ራዕዮች ያንሱናል?

በማንኛውም የኑሮም ሆነ የሥራ ዘርፍ ባለራዕዮች ያስፈልጋሉ። ከተለመደውና ግልጽ ሆኖ ከሚታየው ነገር አልፈው፣ ራቅ አድርገው ማየት፣ መመርመርና መመዘን የቻሉ ሰዎች በብዛት ለምን አይኖሩንም? ከምክንያቶቹ ለመጥቀስ፥

1) ባለ ራዕይ የሆነ ሰው እንደ ሰፊው ሕዝብ “አድርግ” የሚሉትን ብቻ የሚያደርግ፣ “ተናገር” የሚሉትን ብቻ የሚናገር አይደለም። ሌሎች ባልተራመዱበት አዲስ መንገድ መራመድ አስፈሪ ስለሆነ የሚደፍሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ባለራዕዮች የሚሞክሩት ሙከራ ሁሉ ይሰምራል ማለት አይደለም። ብዙ መውደቅና መነሳት አለበት። ይህንን በመፍራት ብዙዎች ባለራዕይ ለመሆን ደፍረው አይነሱም።

2) ባለራዕይ መሆን ብዙ ጉልበት ይጠይቃል። ቁጭ ብሎ ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ አዲስ ሃሳብ ማፍለቅ፣ ረጅም ሰዓት ይጠይቃል። “ይህን ሥራ ሳልጨርስ ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅብኝ ከተቀመጥኩበት አልነሳም” ማለት ትልቅ የሥነ ሥርአት ጉልበት (discipline) ይጠይቃል። ስለ ወደፊት ዕቅድ ማውጣት፣ የማይታየውን የወደፊቱን ማየት አድካሚና ጊዜ የሚፈጅ ነው። ስለሆነም ብዙዎቻችን “ምን አስጨነቀኝ፣ የማላየውን የሩቁን ለማየት ከመሞከር የዛሬውን፣ አጠገቤ ያለውን ብቻ ለምን አላይም” በማለት ባለራዕይ ከመሆን እንሸሻለን።

3) ብዙዎቻችን ባለራዕይ መሆን የሚችሉ ከፍተኛ የተፈጥሮ አንጎል ያላቸው ሰዎች ብቻ እንጂ ለአንደኛ “ተራ” ሰዎች የተሰጠ መስሎ አይሰማንም። በዚህ ምክንያት ብዙዎች የተፈጥሮ ችሎታቸውን በመቀምና ራሳቸውን በማለማመድ ፈንታ “ጊዜያዊ” ሰዎች ሆነዋል። “ራዕይ” አንድ ቦታ የሚቆም ሳይሆን የሚያድግ ነው። ሰዎች በአግባቡ ከተጠቀሙበትና ካለማመዱት ተራ የሚባሉት ሰዎች እንኳ ባለራዕይ መሆን ይችላሉ (መክብብ 10፥10)። እግዚአብሔር በሰጠን ጤናማ አዕምሮ እንድናገለግለው ይፈልጋል።

..........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**